# ፊንፊኔ አዲስ አበባ አይደለም

የወያኔ ትግሬ ኢሕአዴግ መንግሥት ተብዬው ቅጥረኛ ጉጀሌዎች ጥርቅም የሥልጣን እድሜውን ለማራዛም፤ በመላው አገር የተነሳበትን ሕዝባዊ አመጽ ለማርገብ አቅዶ የማደናገሪያ አጀንዳ እየነዛ በወራሪው የፋሽስት ጣሊያን የተወጠነውን የባንቱስታን ክልል ከፋፍሎ መግዛት ስልት፤ ሕወሓት በብቸኛነት የሚዘውረውን የጎሣ ፌደረሊዝም ለማስቀጠል ዘወትር ከሚያደርገው ማደናገሪያ በዐማራውና በኦሮሞው ማኅበርሰብ መካከል ከሚረጨው የጥላቻና ከፋፋይ ቅስቀሳ አንዱ የኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ላይ የልዩ ተጠቃሚነት መብት ረቂቅ አዋጅ ነው።

አስቀድሞ ወያኔ ትግሬ ሕወሓት፣ ኦነግና ሻዕቢያ ተስማምተው ዐማራውን ሕዝብ አግልለው የኢትዮጵያን ምድር በጎሣ መለያ ሸንሽነዋል። ሰፋፊውንና ለሙን ያማራውን ሕዝብ አገርና ምድርን እንዳሻቸው መርጠው ለራሳቸውና ተባባሪዎቻቸው" የኦሮሚያ ክልል፤ የትግሬ ክልል፤ ወዘተረፈ" በማላት ተቀራምተዋል። ዐማራውን ወገን ዐማራ በመሆኑ ብቻ ለይተው ለዘመናት ከሚኖርበት ቀየውና የትውልድ ስፍራው አፈናቅለውታል፤ ያፈናቅሉታል። የወልቃይት ጠገዴ ጠለምት ሕዝብ ዐማራ ጎንደሬ ነኝ በማለቱ ጦር ዘምቶበታል። የባንዳ ውላጅና ማደጎ የሆኑት ወያኔ ትግሬዎች ልክ እንደ ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በቅኝ ለመያዝ በቅድሚያ ያማራ ሕዝብን በተለይም የሸዋ ዐማራ መጥፋት አለበት ብለው የሸዋን ሕዝብ ፈጽሞ ለማጥፋት ያልፈጸሙት አረመኔያዊ ድርጊት ከቶ የለም።

በፀረ ኢትዮጵያዊነቱ ተቀስፎ ድንገት ብግን ያለው መለሰ ዜናዊ የሕወሓት ቅጥረኛ ድርጅት ቀንደኛ መሪ የነበረው ለቀለብ ሰፋሪው የአሜሪካ የስለላ ድርጅት ሲ. አይ. ኤ ዋና ተጠሪ ፓውል ሄንዝ ጋራ በመጋቢት ወር 1982 ዓ.ም በዋሽንግተን ከተማ ባደረገው ቃለ መጠይቅ በግልጽ እንዳስቀመጠው፤

> <<የዐማራ የበላይነትን አንቀበልም ስትል ምን ማለትህ ነው?
> ሠራዊትህ እያለፈባቸውና አየተደገፈበቸው ያሉ እንደ ላስታ፣ ጋይንት፣ ዐማራ ሳይንት፣ ወዘተረፈ ያሉት አካባቢዎች የዐማራ ሕዝብ የሚኖርባቸው እንደ መሆናቸው የእናንተን እንቅስቃሴ ይህ ሕዝብ እንዴት ይመለከተዋል? የሚል ጥያቄ ቀርቦለት የሰጠው ምላሽ
> " የነዚህ አካባቢዎች ሕዝብ ዐማራ የተጨቆነ ሕዝብ ነው። ስለ ዐማራ የበላይነት ስናወራ የምናወራው ስለ ሸዋ ዐማራ የበላይነትና ባለፉት የመቶ ዓመታት ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባን ማዕከል አድርጎ ስለተገነባው ስለዚህ ዓይነት የበላይነት ነው">>
> ሲል እንደመለሰለት ተዘግቧል።

ስለዚህም ነው ጥንታዊው የሸዋ ክፍለ ሀገር በወያኔ ትግሬዎችና ተባባሪያቻቸው ኦነግ ተሸንሽኖ ከኢትዮጵያ ካርታ ላይ የተፋቀው። ስለሆነም ነው የአዲስ አበባ መዲና አካልና ግዛት የሆኑ ክፍለ ከተሞችና ስፍራዎች ሁሉ ተጠቃለው ለኦሮሚያ ክልል ተብዬው የተሰጡት። ስለዚህም ነው የአዲስ አበብ ከተማ ነዋሪ ማኅበረስብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብትና ነፃነቱን ተገፎ በወያኔ ትግሬና ተለጣፊዎች ቅኝ ተገዥ ተደርጎ የሚገኘው። ወያኔ ትግሬዎች በወረሪነት ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ የአዲስ አበባ ከተማን ከፍተኛ ሃብትና ንብረት ዘርፈዋል። አንድ የመድኃኒት ፋብሪካ ቢኖርም እንኳ ይሕንኑ ወያኔዎች ነቅለው ወደ ትግሬ ወስደውታል። የከተማዋ የአንበሳ አውቶቢሶች ወደ መቀሌ ተወስደዋል። በአጠቃላይ ነባሩ የአዲስ አበባ ነዋሪ ከቤት ንብረቱና የግል ይዞታው እንበለ ሕግ በገፍ እየተፈናቀለ ለትግሬዎችና ተለጣፊዎቻቸው እንዲሁም ለውጭ አገር ከበርቴዎች በሊዝ ተቸብችቧል።

ከሩብ ምዕተ ዓመት በላይ የአዲስ አበባ የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊና ማኅበራ- ጭቆና በወያኔ ትግሬዎችና ተለጣፊዎቹ የወረሞ ካድሬዎች ተፈጽሞበታል ይፈጸምበታል። የሰብአዊ መብት ጥሰቱ፣ ሕዝቡን ሆን ተብሎ የማስራቡና ለከፍተኛ ድህነትና ለቀሳፊ በሽታ እንዲጋለጥ መደርጉ ሳያንሰው ይኸው ወያኔ ትግሬ ከተማዋን አጠቃሎ እስከ ስምንት ሚሊዎን የሚደረሰውን አዲስ አበቤ ለኦሮሞ ጎሣ ብሔረተኞች መፈንጭያን ለማስረከብ ሰሞኑን ወያኔ ትግሬና ጀሌዎች ተባብረው የኦሮሚያ ልዩ ጥቅም በአዲስ አበበባ ላይ ረቂቅ አዋጅ አውጥተው ለማጽደቅ ሽር ጉድ እያሉ መሆናቸው ታውቋል።

ያዲስ አበባን ከ80% በላይ ዐማርኛ ተናጋሪ ሕዝብ በአዋጅ አስገድዶ ኦሮምኛ እንዲናገር፤ ትምህርት ቤቶች፤ አደባባዩችና ሰፈሮች የኦሮሞ ብሔረተኞች በፈጠራ ባወጡት ስሞች እንዲሰየሙ፣ ከሁሉም በላይ የከተማዋ ስም <u>ፊንፊኔ</u> ተብሎ እንደሚጠራ በረቂቅ አዋጅ አሳውቀዋል። በወረሞ ብሔረተኞችና ነፃ አውጭዎች ማቀንቀን የሸዋ ምድር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በወረሞ ወይም ጋላ ጎሣዎች ብቻ የሚኖሩባት እንደሆነ አስመስለው በሉባ የደፈጠ ውጊያ ስልት በወረራ በቅርብ ያውም በ17ኛው ክፍለ ዘመን ከደቡብ ምሥራቅ ቦረና ኬኒያ ጠረፍ መጥተው መስፈራቸውን ሸፍጠው ነባር ሕዝብ እንድሆኑ አስመስለው በሚነዙት በሬው ላም ወለድ የፈጠራ ተረት ያዲስ አበበባ ስም አይቀየረም። አዲስ አበባ የኢትዩጵያ ዋና ከተማ ሆና ከመቶ ሠላሣ አምስት ዓመታት በለይ ሆኗታል። ከትንሽ የሸዋ ከተማነት ወደ ትልቅ ዓለም አቀፍ የአፍሪቃ አህጉር ከተማነት አድጋለች።

# ስለ ፊንፊኔን

ታሪካዊና ጅኦግራፊያዊ ሰንድ በጥቂቱ ማቅረብ ወቅታዊ በመሆኑ በአጭሩ ለማቅረብ ተገደናል። በአለፈው ወር የሐረር ወርቅ ጋሻው <u>ፊንፊኔ መንደር እንጂ ከተማ አልነበረም</u> በሚል ርእስ ጥሩ መልስ ስለሰጠችበት እዚህ ላይ መድገም አያስፈልግም።

ዳሩ ግን የወረሞ ብሔረተኞች እንደሚያናፍሱት ፊንፊኔ የሚባል እንኳን ከተማ አንድም ትንሽ መንደር ዛሬ አዲስ አበባ በምትገኝበት ስፍራና አካባቢ (እንዶጥና ) ያልነበረ መሆኑን በአጽንኦት እንገልጻለን። ከዚህም ሌላ ፊንፊኔ የተሰኛ የቱላማ ወረሞ ጎሣ በጭራሽ አይታወቅም። ጀርመናዊው አይከ ሀበርላንድ ስለ ጋሎች ባሕልና ጎሣዎች ሰፊ ጥናት ሲያደርግ ( In the hreart of Ethiopia, in regions once inhabited by Amhara, live the Shoa Galla, often reffered to as Tulama. (E.Haberland: Galla- Süd-Äthiopien, Stuttgart , 1963, P.786)) ሐበርላንድ የሸዋ ጋላ ቱላማ ከሚባል አባት የሚወለዱት ጎዋዎች ገላን፣ አዳ፤ አዳ ዋዩ፤ አቡ፣ ሊበን፤ ሜታ፤ በቾ፤ ጅሩ፤ ያያ፤ አቢቹና ጅዳ ሲሆኑ እንዲሁም ቶርባን ኦቦ ማለትም ሰባት ኦቦዎችን ማለትም ጊምቢቹ፤ ጉለሌ፣ ሰላሌ፤ ኤካ ወበሪ፤ በዲ፤ እና ሙሎ ናቸው።

የብሪታኒያ ንግሥት ቪክቶሪያ መንግሥት ልዑካን መሪ ሻምበል ሐሪስ ወደ ሸዋው ንጉሥ ሣህለ ስላሴ (1813-1847) ተልኮ ለ18 ወራት በሸዋ ቆይቶ፣ የንግድ ውል ስምምነት በአንኳለለ ከተማ ላይ ተፈራርሞ ሲመልሰ መጻሕፍ ጽፏል። (W.Harris: Highlands of Ethiopia (London, 1844) )

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ባመት ሦስት ጊዜ ዘመቻ እያደረጉ በግራኝ ጊዜ ተነጥሎ በደቡብና ምዕራብ ተብታትኖ የሚኖረውን ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ አንድ ለማድረግ፣ ያባቶቻቸውን ጥንታዊ ሃብትና ቅርስ ለማግኘት መሆኑን ሻምበል ሃሪስ ሰምቶ በመጽሐፉ ከፍ ብሎ የሰፈረውን መዝግቦታል። (W.Harris: Highlands of Ethiopia (London, 1844, P. 134) )

የንጉሡ ሠራዊት የአዋሽ ወንዝ ተሻግሮ በምድረ ጉራጌ ሰዶን፣ የአይመለል አካባቢን፣ ከረዩን፣ ጅሌንና ሌሎች ጎሣዎችን አስገብሯል ይላል። ክራፍም ቢሆን ይህንኑ ሁኔታ ጽፎታል። በቅርቡ ወደ ጉራጌ ታላቁ ሕይቅ (የዟይ ሐይቅ) ዘመቻ አደርጋለሁ። በሕይቁ ውስጥ ብዙ ደሴቶች ይገኛሉ። ያያት ቅድምያቶቼ ግምጃ ቤቶችን ይዘዋል። በወርቅ የተሞሉ እንስራዎች፣ ከዝሖን ጆሮ ቆዳ የተሠሩ አርባ ነጋሪቶች፣ ብዙ ታቦቶችና ሰባት መቶ የግእዝ መጻሕፍት በብል መበላት ለአደጋ የተጋለጡ መሆናቸው ታውቋል...። ምንም ተቃውም አይጠበቅም። ነዋሪዎቹ አብዛኛው ክርስቲያን መነኮሳት ናቸው፣ ብዙ ጊዜም ጋብዘውኛል።

<< It is my intention shortly to undertake an expidition to the great lake in Gurage. In it be many islands which contain the treasures of my ancestors: There are jars filled with bracelets of solid gold. There are forty drums made of elephants' ears, and many holy arks pertaining unto ancient churches, besides seven hundred choice Ethiopic volumes, ...No resistance is to be anticipated, for the inhabitants, who are chiefly

Christian monks, have ioften invited me. I must no longer delay to recover the lost wealth of my forefathers. ..>>

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ እንግሊዞቹ ጀልባ እንዲሰሩላቸው እንደጠየቁት ሻምበል ሐሪስ ዘግቧል።

በዚሁ ጊዜ ሸዋ ገብተው ከነበሩት የፕሮቴስታንት ሚሲዎን ተብዬ ሰላዮች እነ የሐን ክራፍና ኢዘንበርግ ይገኙበታል። አፍቃሪ ጋላ የነበረው ክራፍ የጋላ ጎሣ ለራሱና ለሚኖርበት ስፍራ መጠሪያ ስለሌለው ኦሮሚኒያ ተብሎ እንዲጠራ እንዳሳሰበ ይታወቃል። እነ ክራፍ ከሰሜን ኢትዮጵያ ሲባረሩ ነው ወደ ሸዋ በታጁራ በኩል የገቡት።

ዮሐን ሉድቪህ ክራፍ በሸዋ ቆይታው ስለጋሎችና የደቡብ ምዕራብ ጎሣዎችና መልካምድር ሰፊ መረጃ ሰብስቧል። ለምሳሌ አንኮበር ላይ ከተገኛቸው ከምደረ ጉራጌ የመጡት ቄስ ሳዕከ ማርያምን ጠይቆ እንደ መዘገበው በምድረ ጉራጌ ከሰላሳ ሰባት በላይ ገዳማት ይገኛሉ። በከምባታም አውራጃ ከአሥራ አምስት በላይ ገዳማት ሲኖሩ በወላሞም ብዙ ክርስቲያኖች እንደሚኖሩ ነግረውታል። (J.L Krapf: Travels, Researches and Missionary Labour During an eighteen years Residence.. ( London, 1968) 2nd ed, PP. 97-100)

ዮሐን ክራፍ ፊንፊኔ ስለሚባል የጋለ ጎሣ መኖር አልጻፈም። በሸዋ መንግሥት ሥር ያሉትን አሥር ጎሣዎችና ያልሆኑትንም የብዙ ጎሣዎች ስም ዝርዝር መዝግቦታል።

ሻምበል ሃሪስና ቡድኑ በአንድ ወቅት የንጉሡን የማስገበር ዘመቻ ጉዙ ተሳታፊዎች ነበሩ። የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ሠራዊት ከመንዝ፣ ከይፋት፣ ከተጉለት በተቀዳሚ አንጎለላ ላይ እንደተሰበሰቡና ወደ ዘመቻው ሲያመራ የጋራ ጎርፎን ተራራ ሰንሰለት ከአለፈ በኋላ ተጨማሪው ሠራዊት ከጠራ፣ ከቡልጋ፣ ከምንጃር ከወግዳ፣ ከጅሩና ከመራቤቴ ከመጡት ጋራ በመሆን በስተምዕራብ ሰላሌ በሙገርና አባይ ወንዝ መካከል የሚገኙትን ወንዞች እነ ከረንዛ፣ ፊንጭያ፣ ጭያቲ እና ሩፊ ወንዞችን አቋርጠው በመሄድ ግብር አንከፍልም ብለው ወደ አመጹት ከዛሬው ጊንጪ በስተሰሜን አካባቢ በሚኖሩት የሰርቲ ጋላ (Serite Galla) ጎሳዎችን ለመስገበር እንደነበረ የሻምብለል ሐሪስ ዘገባ ያስረዳል።

በሐሪስሪስ ገለጻ በፊንፊኔ ሸለቆና በኤካ ሸለቆ መካከል 50 ማይል ወይም 80 ኪሎ ሜትር ርቀት ለ14 ሰዓታት ተጓዝን ይላል።

<<' During fourteen hours passed in the saddle, above fifty miles of country had been passed over, and the weary forces finally halted in the **Ekka** valley.'  W. Harris: Highlands of Ethiopia, London, 1844,Volume two - Chapter Twenty three>>

የእንጦጦ ተራራ መሸሻ ምሽግነትን ገልጾ የካ ሸለቆ አምባ ላይ አዳር እንደተደረገ በማግስቱ ደግሞ ከረጅም ጉዞ በኋላ ወደ ሱሉልታ ሞሎ ፈልዳ አጠገብ የሸሹትም ተደመሰሱ

( 'A long march the preceding day had brought it to **Sululta** near to Moolo Falda,..')

እያለ ጽፏል።

ሻምበል ሐሪስ በአንድ በኩል የፊንፊኔን ሸለቆ ጥቅጥቅ ያለ ደንና የወንዞች ፏፏቴዎችን ውብነት፤ በሌላ በኩል በሜዳው ላይ ስለነበረው ድርስ ሰብልና መኖሪያ ቤቶች መጋየት፣ በፊንፊንኔ ሸለቆና እና ኤካ ሸለቆ መከከል ያለውን ርቀት 80 ኪሎሜትር ሜትር ተጉዘው፤ በጣም ጥልቅ የሆነውን የወንዙን መልካ በከፍተኛ ችግር ሰውና ከብቱ የመሻገራቸውን አስቸጋሪ ሁኔታ የተረከውን ስናገናዝበው ከቶ በምንም ዓይነት የፊንፊኔ ሸለቆና ጭያካ ዛሬ አዲስ አበባ በምትገኝበት ስፍራ ከእንጦጦ ተራራ በስተደቡብ ሊሆን በጭራሽ አይችልም።

የፊንፊኔ ሸለቆ ተብዬው ሊኖር ቢችል እንኳ ከእንጦጦ በስተሰሜን ምዕራብ ከመገር ወንዝ እና ጊንጪ ወዲህ አዲስ ዓለምና ሆለታ መካለል በሚገኘው አካባቢ ነው። የፊንጭያን ወንዝ ተሻግሮ የተደረገ ዘመቻ በዛሬው እንጦጦ ተራራ አቅራቢያ ሊሆን ከቶ አይቻልምና። ከእንጦጦ ተራራ በስተሰሜን የአዲስ አበባ ግዛት ወሰን ከሙገር ወንዝ በስተቀር ሌላ ትልቅ ወንዝ የለም። ከአዲስ አበባ ወደ አዋሽ የሚፈሱት ወንዞች እነ አቃቂ፣ ወዘተረፈ በጣም ትናንስ ወንዞች እንጅ ሻምብለ ሓሪስ እንደገለጸው ዓይነት ትልቅ ወንዝ ያለመኖሩ ሌላው ማስረጃ ነው። በተጨማሪም የሓን ክራፍም ስለፍንፊኔ ጎሣም ሆነ መንደርነት አልመዘገበም።

የፊንፊኔና ኤካ ሸለቆዎች በመካከላቸው ባለው ርቀት አንጻር ከዛሬው እንጦጦ ተራራ በስተሰሜን ምዕራብ አቅጣጭያ ከመናገሻ ተራራ በስተምዕራብ ሰሜን ከጊንጪ ወዲህ በአዲስ ዓለም ሁለታና ሙገር ወንዝ መካከል የሚገኘው አካባቢ እንጅ ዛሬ አዲስ አበባ (እንዶ ጥና) በምትገኝበት ስፍራ ፊንፊኔ የሚባል ሸለቆና ደን ያልነበረ መሆኑን በትክክል ማረጋገጥ ይቻላል። አዲስ አበባ ከተመሠረተች በኋላ የጉለሌ ሰፈርም ከሰላሌ አውራጃ ጉለሌ የመጡት ሰፋሪዎች ሰፈር ነው። ዛሬም ቢሆን በሰላሌ አውራጃ ውስጥ ጉለሌ የተባለ ቀበሌና መንደር መኖሩ የተረጋገጠ ነው። አዲስ አበባ በመጀመሪያ የሸዋ ዋና ከተማ ቀጥሎም የመላው ኢትዮጵያ መዲና ከሆነችበት አንስቶ ከየክፍለ ሀገራቱና አውራጃዎች እንደመጡት ማለትም ልክ ከይፋትና መንዝ፣ ከተጉለትና ቡልጋ፣ ከመራቤቴ፣ ከጎላ፣ ከሞረት፣ ከጎጃም፣ ከወሎ፣ ከጉራጌ፣ ከትግሬ፤ ከጋሞ፤ ከሰሜን በጌምድር፤ ከሐረርጌ ከጋሞ ጎፋ፤ ከከፋ፣ ወዘተረፈ መጥተው በአዲስ አበባ ለሚኖሩበት ሰፈራቸው ስም እንደሰየሙት ማለት ነው።

እራሳቸውን የኦሮሞ ጎሣ ነፃ አውጭ ያደረጉት ፀረ ዐማራ ቡድኖች ቆርጠው ሲቀጥሉ <<የጉለሌ ነባር ነዋሪዎች ከፊንፊኔ ከተማ በምኒልክ ዘመን ተባረሩ>> እያሉ ዓይናቸውን በጨው አጥበው ይወሻከታሉ። በየረር፤ በዝቋላና በእንጦጦ ተራሮች መካከል ያለው ገርማማ እና የመናገሻ አውራጃ በጠቅላላው የሸዋ መንግሥት ግዛት የሆኑት ከአጤ ምኒልክ መንገሥ 80 ዓመት አስቀድሞ ነው። ምኒልክ ከእነዋሪ ወደ እንጦጦ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ከተማ መጥተው ከሠፈሩ በኋላ ከተራራው ወርደው ወደ ግቢ ፍል ውሃ አናት ላይ በእቴጌ ጣይቱ ቡጡል አዲስ አበባን ሲቆረቁሩ አንድም የተባረረ ሰው የለም። ለምንስ ይባረራል? ያዲስ አበባን ፍልውሃ ምንጭ ከሁሉ በተቀዳሚ ያገኙት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ናቸው። እሳቸውም የየካ ሚካኤልንና የአቃቂ መድኃኔዓለምን እንዲሁም፣ የመናገሻ ማርያምን ቤተክርስቲያናትን ተክለዋል። በሁለተኛ ደረጃ ፍል ውሃውን ያገኙት እቴጌ ጣይቱ ቡጡል ናቸው። በሌላ በኩል ሻምበል ሐሪስ ይሁን ወይም ሌላ ፈረንጅ ወይም አበሻ አካባቢውን የጎበኙት ሰለ ፍል ውሃው ምንጭ ምንም ያሳወቁት ነገር የለም።

ሌላው የኦሮሞ ጎሣ ብሔረተኞች ማወናበጃ የአዲስ አበባን ፍል ውሃ ፊንፊኔ ከሚባል የሌለ የጋለ ጎሣ መጠሪያ ስም ጋራ አንድ አድርገው ያነበንባሉ። ያንድ ፍልውሃ ምንጭን ያውም ያማርኛ መጠሪያ ስም ፊንፊኔን እንዴት ጋልኛ እንዳደርጉት የሚታወቅ ነገር የለም። ወያኔ ትግሬና ኦነግ ባደረጉት ስምምነት ያዲስ አበብ ከተማ አካላትን እነ ገፈርሳ፣ ሰበታ፣ ዓለም ገና፣ ስሉልታ፣ ሰንዳፋ፤ መናገሻ፣ ለገዳዴ፣ አባ ሳሙኤል ወዘተረፈ ለኦሮሚያ ክልል ተብዬው ያለ አግባብ በመክለል ነበር። አሁን ደግሞ ቀሪውን የአዲስ አበባ ከተማ አጠቃለው የባንቱስታን አሮሚያ ክልል ተብዬው ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር ለማድረግ አስበው ነው የልዩ ጥቅም ማስገኛ ረቂቅ አዋጁ ያወጡት። በአዲስ አበባ ሕዝብ ኪሣራ ለማትረፍ በታቀደው ስሌት እንደተመለከተው ጥንታዊ ፊንፊኔ ከተማቸው አዲስ አበባ ከመምሥረቷ በፊት የነበሩት ሰፈሮች፣ መንገዶች፣ አደባባዮች ወዘተረፈ ይጠሩት የነበረውን የጋልኛ ስማቸውን በልበ ወለድ ፈጠራ ሰይመው ያዘጋጁትን የሰም ዝርዝ በርረቂቅ አዋጁ መግቢያ ላይ ተመልክቷል:::: ይኸስ መቼም ከንቱ ቅዠት እንጂ ሌላ ምን ልባል!

አስገራሚው ጉድ ደግሞ የኦሮሞ ጎሣ ብሔረተኞነት አቀንቃኞች በዐማራ ሕዝብ የተሠሩትን ታላላቅ ከተሞች ለመያዝ እንጂ በራሳቸው አንድም ከተማ በሩብ ምዕተ ዓመት ውስጥ ወያኔ ትግሬ መቀሌን ከተማ ከመላው ኢትዮጵያ እየዘረፈ እንደገነባው ዓይነት እንኳ ሳይገነቡ ያማራ ከተሞችን ብቻ ከወያኔ ትግሬ ጋራ ወግነው በአቋራጭ በአዋጅ ለማግኘት ማዘጥዘጣቸው ነው።

የአዲስ አበባ ከተ ሕዝብ ነፃነት ይረጋገጣል!!

በነጻ ዴሞክራሲያዊ ምርጭያ የራሱን አስተዳደር ይወስናል::!

የወያኔ ትግሬ ባንቱስታን ፌደራሊዝም፤ የጎሣ ክልልና ሕገመንግሥት ይወድቃል!!!

ቅጥረኛው ወያኔ ትግሬና ግብረአበሮቹ ሁሉ ድባቅ ይመታል፤

ኢትዮጵያ ከባንቱስታን አፓርታይድ ነፃ ትወጣለች!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

ገለበው ሰንጎጎ ዘብሔረ ጋሞ

---